ዳግመኛ መወለድ

ቸርነት አማኑኤል

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

ዳግመኛ መወለድ ማለት ምን ማለት ነው?

ዳግም ልደት ከክርስትና ዋነኛ ትምህርቶች መካከል አንዱ ነው። የሰው ልጅ ሁለት ልደቶች አሉት። አንደኛው ከሰጋ ፈቃድ በሩካቤ ከእባት እና ከእናት የሚያገኘው ስጋዊ ልደት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ኢየሱስን በማመን እና በመቀበል የሚያገኘው መንፈሳዊ ልደት ነው፣ ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም (ዮሐንስ ወንጌል 1፡12-13)።

ያለዚህ ልደት ሰው የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርስ አይችልም። ሰው በስጋ ልደቱ የሰው ልጅ እንደሚባል፣ በመንፈስ ልደቱ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። ስጋ እና ደም የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርሱ አይችሉም፣ የእግዚአብሔር ልጆች ግን የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርሱ ይችላሉ። የመጀመሪያውን ልደት ብቻ ያገኙ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውሰጣቸው የለምና ስጋ እና ደም ብቻ ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርሱ አይችሉም፣ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም (1ቆሮንቶስ 15፥50)።

የመጀመሪያውን ልደት ብቻ ያገኙ ፍጥረታዊ ሰዎች ይባላሉ። አካላቸው ደግሞ ፍጥረታዊ አካል ይባላል (1ቆሮንቶስ15፡46)። እነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ነገር ሊያስተውሉ አይችሉም “ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ሰለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም (1ቆሮንቶስ 2፡14)።

የመጀመሪያውን ልደት በመወለድ እንዳገኘነው፣ ሁለተኛውንም ልደት በመወለድ እናገኘዋለን። የመጀመሪያውን ስጋዊ ልደት ስጋዊ ከሆኑ ቤተሰቦቻችን እናዳገኘነው ሁለተኛውን ልደት ደግሞ መንፈሳዊ ከሆነው አባታችን በመወለድ የምናገኘው ይሆናል። የመጀመሪያውን ልደት መልካም ሰው በመሆን፣ ምጽዋት በመስጠት፣ በመፀለይ እና በመጾም እናዳላገኘነው፣ ሁለተኛውንም ልደት በእነዚህ መንገዶች እናገኘውም። የቤተሰቦቻችን ልጅ ለመሆን የከፈልነው ክፍያም ሆነ አስተዋጽዎ እንደሌለ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆንም የምናዋጣው መዋጮ የለም።

የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ከእኛ የሚጠበቀው አንድ ነገር ብቻ ነው። ይኸውም፣ በኢየሱስ ማመን እና እርሱን መቀበል፣ ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም (ዮሐንስ ወንጌል 1፡12-13)። በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና (ገላቲያ 3፡26)።

የሰው ልጅ ሁለተኛውን ልደት ካላገኘ ወይም ዳግም ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርስ አይችልም፣ ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው (የዮሐንስ ወንጌል 3፡5-6)። ምንም ይሰራ ምን፣ ከስጋ የተወለደ ስጋ ነው። ስጋ እና ደም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊወርሱ አይችሉም። የተፈጥሯዊ ሰው መልካምነት እስከ አለም ዳርቻ ቢሰማም እንኳ፣ ከስጋ ከተወለደ ስጋ ብቻ ነው። ድርጊቱ ምንም ያህል የተከበረ፣ እንቱ የተባለ እና የተመሰከረለት ቢሆን፣ ተፈጥሮውን አይቀይርለትም።

ሃይማኖተኛ ቢሆን፣ አዘውትሮ ረዥም ፀሎት ቢያደርግ (ማቴዎስ 23፡14) በሳምንት ሁለት ጊዜ ቢጾም ሳያጓድል ለእግዚአብሔር አሰራት ቢያወጣ (ሉቃስ 18፡12)፣ ቀማኛ፣ ዓመፀኛ አመንዝራ ባይሆን (ሉቃስ 18፡11)፣ በሌላ

አባባል በሰፈሩ የተመሰከረለት የሞራል ሰው ቢሆን፣ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ያው ሰጋዊ፣ ያው ፍጥረታዊ ብቻ ነው።

ዳግም ልደት (ደኅንነት) በራሱ የሚሆን ነገር ሳይሆን የሰዎችን ስሜትና አቀባበል የሚሻ ነው። ለመዳን የሚፈልጉ ሰዎች በኢየሱስ ማመን አለባቸው። ማመን ያለባቸው ምንድን ነው? ኢየሱስ ኃጢአታቸውን በመሰቀል ላይ እንደ ተሸከመ ማመን አለባቸው። ምክንያቱም በእነርሱ ምትክ ሞቷል። ስለዚህ ከእነርሱ የሚጠበቀው በምትካቸው የሞተውን ኢየሱስ ማመን ብቻ ነው። ድኅነትን (ደኅንነትን) ለማግኘት የተለየ የመዳኛ ሥራ መሥራት አይጠበቅባቸውም። ይህን ጊዜ ሰው ክርስቲያን ሆኖ ይወለዳል የሚለው የተሳሳተ አመለካከታቸው ይወገዳል። የድኅነት (የደኅንነት) ተሰፋቸው ሁሉ የሚያርፈው ኢየሱስ በመሰቀል ላይ የፈጸመላቸውን ሥራ በማመን ብቻ ይሆናል። የዮሐንስ 3:3-5

በእግዚአብሔር መንግስትም እድል ፈንታ የለውም። ዳግም ልደት የእግዚአብሔር ምህረት ውጤት እንጂ የእኛ መልካም ሰራ ውጤት አይደለም። እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ሰላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም (ቲቶ 3፡5)። በመልካም ሰራ ተፈጥሯችን አይቀየርም። መልካም ሰራችን በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሚኖረው ከአዲሱ ተፈጥሯችን ሲመነጭ ብቻ ነው።

ዳግም ልደት ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም ሲፈጠር ወይም ሲለወጥ የሚከናወን መንፈሳዊ ድርጊት ሲሆን ይህም ድርጊት ሰው ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕሪይ ተካፋይ እንዲሆን ያስችለዋል፣ ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተሰፋን ሰጠን (2ጴጥሮስ 1፡4)።

ኢየሱስን በማመን እና በመቀበል የተገኘው ልጅነት (ዮሐንስ 1፡12)፣ እግዚአብሔርን አባት ብለን እንድንጠራው እና የእግዚአብሔር ወራሾች እንድንሆን መብትን አሰገኝቶልናል፣ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀበላችሁምና። የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል። ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም ደግሞ እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን (ሮሜ 8፡14-17)።

በመጀመሪያው ልደት ከቤተሰቦቻችን (ከፊተኛው አዳም) የወረስነው ተፈጠሮ፣ አዳማዊ ተፈጥሮ ወይም አሮጌው ሰው ይባላል። በዳግም ልደት ኢየሱስን በማመን ከእግዚአብሔር ያገኘነው አዲሱ ተፈጥሮ ደግሞ አዲሱ ሰው ይባላል፣ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል (ቆላሲያስ 3፡9-10)። ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል (2ቆሮንቶስ 5፡17)።

ኢየሱስን አምኖ የተቀበለ ሰው፣ በዳግም ልደት ሌላ አዲስ ተፈጥሮ ስለሚኖረው የሁለት ተፈጥሮዎች ባለቤት ይሆናል ማለት ነው። በዳግም ልደት አዲስ ተፈጥሮን እናገኛለን እንጂ የቀድሞውን አሮጌ ተፈጥሮ አናጣም። አሮጌው ተፈጥሮ እስከሞታችን ከእኛ ጋር ይኖራል። እነዚህ ሁለት ተፈጥሮዎች በባህሪይ ተቃራኒ በመሆናቸው እርስ በእርሳቸው ይቀዋወማሉ፣ 5፥17 ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ (ገላቲያ 5፡17)።

ዳግም የተወለደ ሰው በፊተኛው እና እግዚአብሔርን በማያከብረው ሰጋዊ ወይም አሮጌ ተፈጥሮ ቁጥጥር ስር እንዳይሆን በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እለት እለት መታደስ ይኖርበታል። የአዲሱ ተፈጥሮ ምግብ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ማቴዎስ 4:4)። የአሮጌውን ተፈጥሮ ፍላጎት እንቢ እያልን የአዲሱን ተፈጥሮ ፈቃድ እየተቀበልን የምንጓዘው ጉዞ የቅድስና ጉዞ ይባላል፣ ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት

የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድሰና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።

ሰው በአሮጌው ተፈጥሮ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ስለማይችል ዳግም ልደት ያስፈልገዋል፣ እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ (መዝሙር 51:5)። የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል? (ኤርሚያስ 17:9።) “ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም (ሮሜ 8:16-17)። በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን (ኤፌሶን 2:3)።

ዳግመኛ ልደት ያገኘ ሰው ምልክቶች ምንድን ናቸው? ዳግም የተወለደ ሰው ከሃጢአት ልምምድ ነፃ የወጣ ነው (ሮሜ 6:14-23)። ዳግም የተወለደ ሰው የእግዚአብሔርን መንፈስ ምሪት ለመቀበል እና ለመታዘዝ መሻት ይኖረዋል (ሮሜ 8:13-14)። ዳግም የተወለደ ሰው የጽድቅ ሕይወት ይኖረዋል (1ዮሐንስ 2:29)። ዳግም የተወለደ ሰው ሌሎችን ይወዳል (1ዮሐንስ 4:7)። ዳግም የተወለደ ሰው ከሃጢአት ሕይወት ይርቃል (1ዮሐንስ 3:9፤ 5:18)። ዳግም የተወለደ ሰው አለምን መውደድ ይተዋል (1ዮሐንስ 2:15-16)።

ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መሰክሮ ይድናልና። ሮሜ 10:9-10

(ሮሜ 10:5-13)። ጳውሎስ ሁለት የድነት (ደኅንነት) መንገዶችን ለማነጻጸር ሲል ብሉይ ኪዳንን ይጠቀማል። የመጀመሪያው፥ አይሁዶች ድነትን (ደኅንነትን) ለማግኘት የሚያስችል በጎነት ለመቀዳጀት ያደረጉት ጥረት ነው። ዘሌዋውያን 18:5 እንደሚለው፥ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሕግጋቱን ሙሉ በሙሉ መፈጸም ያስፈልጋቸው ነበር። ነገር ግን ይህ ለሁሉም ኃጢአት የሚሠራ አለመሆኑን ጳውሎስ ቀደም ብሎ አመልክቷል። ስለሆነም፥ መንፈሳዊ ሕይወት ሕግጋትን ከመከተል ሊገኝ አይችልም።

የእግዚአብሔር የሆነው ሁለተኛው የድነት መንገድ ግን ከፍተኛ ብርታትንና ተአምራትን አይጠይቅም። ወደ ቅዱስ ሰፍራዎች የሚደረጉ ረዣዥም ጉዞዎች ለድነት ሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አይኖርም። የእግዚአብሔር ድነት ሰዎች ሁሉ ይቀበሉት ዘንድ በአጠገባቸው አለ። ድነትን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ ይልቅ ማመን እንደሚያስፈልግ ጳውሎስ አብራርቷል። ክርስቶስ የኃጢአታችንን ቅጣት የከፈለ የግል መሥዋዕታችን እንደሆነ ከልባችን ማመን አለብን። እንዲሁም ክርስቶስን እንደ ጌታችን ለመከተል ቆራጥ ውሳኔ ማድረግ አለብን። ይህ ውስጣዊ ተግባር በኃፍረት ተሸማቅቀን ከሰዎች የምንደብቀው ዓይነት ሳይሆን፥ በይፋ የሚታወጅ ነው። እንድ አይሁዳዊ ወይም አሕዛብ ይህን ቀላልና ነገር ግን ሕይወት ለዋጭ ውሳኔ በሚያደርግበት ጊዜ የእግዚአብሔር ጽድቅና በረከት ሕይወቱን ይሞላዋል።

ጠቅለል ሲደረግ ዳግመኛ መወለድ

ትልቅ ትኩረት ይሰጥበት !!

- **ከክርሰቲያን ቤተሰብ ሰለተወለደ እንድ ሰው በውርሰ የሚያገኘው ነገር አይደለም። ዮሐንስ 3:3-8**
- **ዳግም ልደትን ሰው በቤተክርሰቲያን በማደግ እና ሰለ ኢየሱስ ክርሰቶስ ሞት እና ትንሳኤ በማወቅ የሞያገኘው ነገር አይደለም። ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ። 1ኛ ጴጥሮስ 1፥23**
- **ዳግም መወለድ ማለት ቤዛነትን ማግኘት ነው። ቤዛነትን ማግኘት ማለት በመንፈስ ቅዱስ በሆነ መታደስ የመንጻትን ሥርዓት የማሰፈጸም ማለት ነው። ቲቶ 3:5-8**

- **ቤዛ ቀን ቤተ ክርስቲያን ከገባንበት ቀን ጀምሮ በመንፈሳዊ ሕይወት በቤተክርስቲያን የኖርናቸው ቀናቶች እይደለም። ቤዛ ከቀናቶች እጌዱ ቀን ነው። ያም ቀን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እምነን ጽድቅን ያገኘንበት እና በእጁችንም መስክረን ድኅነታችንን ያሰመዘገብንበት ቀን ነው። ሮሜ 10:8-10**
- **ዳግም ልደት በእምነት ብቻ የሚገኝ እንጂ በመልካም ሥራ፣ ጥሩ መንፈሳዊ ሰው ለመሆን በሚደረግ ጥረት፣ በማህበረሰቡ መካከል መልካም ሥነ ምግባር ያለው ሰው በመሆን፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሳብ በማወቅ አይገኝም።**

======

ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆዲሞስም፦ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው። ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ሰላልሁህ አታድንቅ። ዮሐንስ 3:3-8

ነገር ግን ምን ይላል? በእፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው።ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳሰነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። ሮሜ 10:8-10

እንዲህም አላቸው፦ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።ማርቆስ 16:15-16

ኢየሱስም እንዲህ አለ

“በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው። ዮሐንስ 17፥17

የካቲት 18/2016 ዓ.ም